ፈብሯሪ 6ቀን 2020 ዓ.ም. አዳዲስ መረጃ

ከFairfax County Health Department ጋር በመቀናጀት FCPS በቻይና የተፈጠረውን የጤና ቀውስ በአገራችን ምን አይነት ተጽእኖ እንደሚያመጣ በመከታተል ላይ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት መኖሩ የተረጋገጠበት ኮሮና ባይረስ/coronavirus (2019-nCoV) በሽታ በ Fairfax County ወይም በVቨርጂኒያ ውስጥ የለም። በCenters for Disease Control and Prevention (CDC) መረጃ መሰረት በአሁኑ ወቅት የአሜሪካ ህዝብ ለበሽታው ያለው ተጋላጭነት ዝቅተኛ ነው ። የጤና ክፍሉ/Health Department ስለ ኮሮና ባይረስ የሚናገር handout ጽሁፍ በመልእክቱ አካቷል። በተጨማሪም ስለ አዲሱ ኮሮናባይረስ/coronavirus ወረርሽኝ የሚናገር ጽሁፍ በCDC website ይገኛል።

FCHD አገር አቀፍ ደረጃ ፣ በክፍለ ለሃገሩ እና በአካባቢው ካለው የጤና እና ደህንነት አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት የማህበረሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ እንደየአስፈላጊነቱ ተጨማሪ የማህበራዊ ጤና እርምጃዎችን ለመውሰድ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል። የኮሮና ቫይረስ ሁኔታ መለዋወጡን እየቀተለ እያለ FCPS ከFCHD ጋር እየሰራ የማህበራዊ ጤና ምክረ ሃሳቦችን እየተገበረ በየጊዜው አዳዲስ መረጃዎችን ለማህበረሰቡ ያደርሳል።

ስለ አዲሱ የኮሮና አይረስ (2019-nCoV) በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

1. FCPS በቅርቡ የተከሰተውን የኮሮና ቫይረስ (2019-nCoV) ችግርን ለመፍታት ምን እያደረገ ነው?

FCPS ከFairfax County Health Department ጋር በመቀናጀት በቻይና የተፈጠረውን የጤና ቀውስ በአገራችን ምን አይነት ተጽእኖ እንደሚያመጣ በቅርበት በመከታተል ላይ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት መኖሩ የተረጋገጠበት የኮሮና ባይረስ/coronavirus (2019-nCoV) በሽታ በFairfax County ወይም በVቨርጂኒያ ውስጥ የለም። በCenters for Disease Control and Prevention (CDC) መሰረት በአሁኑ ወቅት የአሜሪካ ህዝብ ለበሽታው ያለው ተጋላጭነት ዝቅተኛ ነው። FCPS ይህንን በትምህርት ቤት ከጤና ጋር የተገናኘ ችግር ለመፍታት ከFCHD ጋር በመስራት መመሪያ ወይም አስፈላጊ ተግባርራትን እየፈጸመ ነው።

2. ልጄ ወይም ከልጄ ትምህርት ቤት ሌላ አንድ ሰው ወደ ቻይና ተጉዞ ነበር ። በቅርቡ ወደ ቻይና የተጓዙ ተማሪዎች ወይም የትምህር ቤት ሰራተኞች በቤታቸው መቀመጥ/መቆየት አለባቸው?

FCPS ከFCHD ጋር በቅርበት በመስራቱ ከማህበራዊ ጤና ሰራተኞች አዳዲስ መረጃዎችን ተቀብሏል። በቅርቡ ለተጓጉች የተቀመተው መመሪያ ጉዞው የማህበራዊ ጤና አገልግሎት ምክረ ሃሳብ መሰረት እና ጉዞው በተፈጸመበት ጊዜ ላይ ተንተርሶ ለውጥ ተደረጎበታል።

- ማንኛውም ከቻይና የተመለሰ እና የትኩሳት፣ ሳል ወይም ለመተንፈስ የመቸገር ምልክት ያሳየ ሰው በቤቱ ተቀምጦ/ቆይቶ የጤና አገልግሎት የሚሰጡትን ወይም የFairfax County Health Department በአስቸኳይ ማነጋገር አለበት።

- ይህ ሰው ከ14 ቀናት በፊት ከቻይና የተመለሰ ከሆነ ሊታመም ከሚችልበት የጊዜ ገደብ ውጪ ስለሆነ ትምህርት ከመከታተል የሚያግደው ነገር የለም።

- አንድ ሰው ከቻይና ወደ አሜሪካ ከፌብሯሪ 2 ምሽት አዲሱ የጉዞ እገዳ ከመውጣቱ በፊት ከደረሰ ትምህርት ከመከታተል የሚያግደው ነገር የለም።

- አንድ ሰው ከቻይና ወደ አሜሪካ ከፌብሯሪ 2 ምሽት በኋላ ከደረሰ በአገር አቀፉ እገዳ ስር ይሆናል። ወደ Wuhan ከተማ ወደ Hubei ግዛት የተጓዘ ሰው ወድያውኑ ለ14 ቀናት ለብቻው እንዲቆይ ይደረጋል። በቻይና ውስጥ በሌሎች ቦታዎች የተጓዘ ሰው እና በመረጃ ከተረጋገጠ ሌላ በኮሮና ቫይረስ ከታመመ ሰው ጋር ግንኙነት ያላደረገ ሰው እራሱን ለይቶ ይቆይ እና በጤና ባለሞያዎች ክትትል ይደረግበታል። በዚህ ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች ከጉዞቃቸው በኋላ ለ14 ቀናት ወደ ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ ይታገዳሉ። ይህ አዲሱ እገዳ በቻይና እየጨመረ በሄደው የኮሮና ቫይረስ ታማሚዎች ቁጥር ጋር በተገናኘ ነው።

3. ቤተሰቤ ከፈብሯርይ 2 በኋላ ከቻይና ተመልሷል ። ልጄ እራሱን ለብቻው ለ14 ቀናት በጤና ባለሞያዎች ክትትል እየተደረገበት እንዲያቆይ ተጠይቋል ። ምን ማድረግ አለብኝ?

በዚህ ወቅት ወላጅ ወይም አሳዳጊ የትምህርት ቤቱን ርእሰ መምህሩን/ሯን ወድያውኑ ማነጋገር እና ተማሪው ቀሪ በሆነበት ጊዜ ሁሉ መደበኛ ግንኙነት ማድረግ አለበት።

4. ቤተሰባችን በቅርቡ ወደ ቻይና ተጉዞ አዲሱ እገዳ በፌብሯሪ 2 ከመውጣቱ/ከመደረጉ በፊት ወደ አሜሪካ ተመልሷል። ልጃችንን ለተወሰነ ጊዜ ከትምህርት ቤት አስቀርተን እቤት እንዲቆይ አድርጌያለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?

የማህበረሰብ ጤና መመሪያ ከፌብሯሪ 2 በፊት ከቻይና የተመለሱ ሰዎች ተለይተው እንዲቀመጡ አያዝም። ነገር ግን FCPS አንዳንድ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች በአዲሱ ኮሮና ቫይረስ ከተጠቁ ቦታዎች የተመለሱ ልጆቻቸውን በቤታቸው ለተወሰነ ጊዜ እንዲቆዩ ማድረግ ይመርጡ ይሆናል። ይህ ውሳኔ የወላጆች ወይም አሳዳጊአውች ብቻ የሆነ ውሳኔ ነው። በዚህ ወቅት ልጆቻቸውን በቤታቸው ለማስቀረት የመረጡ ወላጆች የትምህርት ቤቱን ርእሰ መምህሩን/ሯን ወድያውኑ ማነጋገር እና ተማሪው ቀሪ በሆነበት ጊዜ ሁሉ መደበኛ ግንኙነት ማድረግ አለበት።

5. ወደ ደቡብ ኮሪያ ፣ ታይላንድ ወይም ወደ ሌላ የኮሮና ቫይረስ መኖሩ ወደ ተረጋገጠበት አገሮች የተጓዙ ተማሪዎች ትምህርት መከታተል ይችላሉ?

እነዚህን አገሮች በሚመለከት የተደረገ እገዳ ወይም ተማሪዎች ትምህርት እንዳይከታተሉ የሚያደርግ መመሪያ የለም። በሌሎች አገሮች በአዲሱ የኮሮና ቫይረስ የተጠቁ ሰዎች ቁጥር ብዙ አይደሉም።

6. የተማሪው የቤተሰብ አባላት በቅርቡ ወደ ቻይና ተጉዘው ቢመለሱ ትምህርት መከታተል ይችላሉ?

ተማሪዎቹ ሳይጓዙ ነገር ግን የተማሪዎቹ ቤተሰቦች ወደ ቻይና ተጉዘው በ14 ቀናት ጊዜ ውስት ከተመለሱ እና እንደ ትኩሳት ፣ ሳል ፣ ወይም የመተንፈስ ችግር አይነት የህመም ምልክቶችን ካላሳዩ ትምህርት እንዳይከታተሉ የሚያደርግ እገዳ አይኖርም።

7. FCPS ወደ ቻይና የተጓዙ እና ተመልሰው ትምህርት እንዲከታተሉ የተፈቀደላቸውን ተማሪዎች ወይም ሰራተኞችን ክትትል ያደርጋል?

FCPS የCDC እና US Customs and Border Protection (CBP) /ጉምሩክ (ከፈብሯሪ 2 ጀምሮ) ከፍተኛ የጤና ፍተሻ/ምርመራ ለማድረጊያ መዘጋጀታቸውን ያውቃል። ነገር ኝ FCPS ከአገር ውጪ የተጓዙ ተማሪዎችን ወይም ሰራተኞችን አይመረምርም ። ይህ በፍጥነት ተለዋዋጭ ሁኔታ ስለሆነ FCPS ከFCHD ጋር በቅርበት መመሪያውን እየተከተለ ይሰራል።

8. ልጄ አደጋ ላይ ነው? ልጄን በትምህርት ቤት ደህንነቱ እንዲጠበቅ ምን ማድረግ አለብኝ?

በCDC መሰረት በአጠቃላይ በአሜሪካ ውስጥ ለሚኖሩ ተማሪዎች እና ማህበረሰብ የኮሮና ቫይረስት የጥቃት ደረጃ ዝቅተኛ ነው። የተለየ ጥያቄ ካለ በFCHD የሚገኝ የተላላፊ በሽታዎችን ነርስ በስራ ሰአት በመገናኘት ማናገር ይቻላል። ስልክ ቁጥሩ 703-267-3511 ነው።

በክረምት ወራት የመተንፈሻ አካል ህመም የሚፈጥሩ ሌሎች እንደ ጉበፋን የመሳሰሉት በሽታዎች የተለመዱ ናቸው። ጉንፋን ፣ ሳል ፣ እና ሌሎች የመተንፈሻ አካል በሽታዎች እንዳይዘን የሚያደረጉ ቅድመ ጥንቃቄዎች ጥሩ የመተንፈሻ አካል መከላከያ እና የእጅ ንጽህና መጠበቅ እንደ ሲያስልዎ እና ሲያስነጥሱ መሸፈን ፣ እጅን መታጠብ እና ሲታመሙ እቤት መቆየት ይመከራል።

9. የ FCPS ተማሪዎች እና ሰራተኞች ወደ ቻይና ለመሄድ እቅድ ሊኖራቸው እንደሚችል ወይም የቻይና ተማሪዎች ትምህርት ቤታችንን ሊጎበኙ እንደሚችሉ ሰምተናል ። ይህን እንዴት መቆጣጠር ይቻላል?

የFCPS መመሪያ 3325 የአጭር ጊዜ የተማሪዎች ጉብኝት/ Short Term Student Visitations ርእሰ መምህሮች የአጭር ጊዜ ጉዞ በሚያቅዱበት ወቅት መመሪያ ይሰጣል። የደዚህ ሂደት አካል የሆነው የአደጋ ቅነሳ /Risk Management እና የESOL አገልግሎት ቢሮ የጉዞ ጉብኝት የጊዜ ሰሌዳውን ይከታተላሉ። FCPS በአሁኑ ሰአት ምንም አይነት ወደ ቻይና ወይም ከቻይና የሚደረግ ጉዞ እንደሌለ አረጋግጧል። በአሁኑ ሰአት CDC አላስፈላጊ ጉዞ ወደ አዲሱ ኮሮና ቫይረስ ወዳለበት አገሮች እንዳይደረግ ወደ ቻይና ለሚደረግ የጉዞ ማስጠንቀቂያ አውጥቷል። የተማሪ እና የሰራተኛ ደህንነት ተቀዳሚ ጉዳያችን ነው። FCPS ወደ በኮሮና ቫይረስ ወደተጠቁ ቦታዎች የሚደረጉ ጉዞዎችን አይደግፍም።

10. ጥያቄ ካለኝ ማንን ማናገር እችላለሁ?

ስለ ልጅዎ የትምህርት ክትትል ጥያቄ ካለዎት እባክዎ ትምህርት ቤቱን በቀጥታ ያነጋግሩ።

ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ስለ ኮሮና ቫይረስ ህመም ወይም የበሽታው ምልክቶች ወይም እንዴት የመተንፈሳ አካል በሽታን መከላከል እንደሚቻል ጥያቄ ካላቸው በFairfax County Health Department በሚገኘው የተላላፊ በሽታዎችን ነርስ በስራ ሰአት በመገናኘት ማናገር ይቻላል። ስልክ ቁጥር 703-267-3511 ነው።